## ምስጢረ ሥጋዌ

የአምላክ ሰው የመሆን ምስጢር ማለት ነው። ብዙዎች እግዚአብሔር አዳምንና ልጆቹን ለማዳን
ሰው መሆን ለምን አተጋው? የሚል ጥያቄ ሲያቀርቡ ይሰማሉ። እግዚአብሔር ሥጋን ይዋሐድ ዘንድና ስ
ይጣንን ድል ነስቶ ሰዎችን ነፃ ወጣ ዘንድ ያስፈለገው ምስጢር ፤ አዳምና ሔዋን በገነት በተድላ ደስታ
ሲኖሩ ሳለ ጠላት ዲያብሎስ ቀንቶ በእባብሥጋ ተሰውሮ ወደ እነሱ ዘንድ ቀረበ። አዳምና ሔዋን ስይጣ
ን መሆኑን ሳያውቁ በእባብ ሥጋ ተሰውሮ የመጣው በምክረ ስይጣን ተታለው ትዕዛዘ እግዚአብሔርን ጣሱ
፥ ከእግዚአብሔርም ልጅነትም ወጡ፥ እግዚአብሔርም ከኤደን ገነት አስወጣቸው። የገነትንም ዙሪያ በም
ትገለባበጥ በሱራፌል ስይፍ አስጠበቃት፥ ዘፍጥረት 3፥24።

አዳምና ሔዋን ገነትን የመሰለች ቦታ፥ እግዚአብሔር የመሰለ ጌታ በማጣታቸውና በመንጸፈ ደይ
ን በመውደቃቸው የተነሣ ሌት ተቀን በእንባ ወደ እግዚአብሔር ይምራቸው ዘንድ ይጸልዮ ይጮሁ ጀመር
። እግዚአብሔር አዳም በበደለ እርሱ ሁለተኛ አዳም ሆኖ ስለአዳም ክሶ ከስይጣን ባርነት ነጻ እንደሚያ
ወጣው ቃል ገባለት። ይህንንም የተስፋ ስንቅ ይዞ አዳም ወደ መቃብር ወረደ ነፍሱም በሲኦል።

የስይጣንን ጥበብ ተወዳዳሪ በማይገኝለት ጥበቡ እግዚአብሔር ሊያፈርስ፥ ስይጣን አዳምና ሔዋን
ን እባብ መስሎ ራሱን ሰውሮ መጥቶ እንደ አሳታቸው ሁሉ እርሱም የሥጋዌን ምስጢር ከስይጣን ሰውሮ
የወደቀውንና የተጎሳቆለውንየአዳምን ሥጋ ከስይጣን ባርነት ነጻ ለማውጣት ንጽሕት ከምትሆን ከእመቤታ
ችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ፍጽም አምላክ፥ ፍጽም ሰው ሆነ። ዲያብሎስም አምላክ መሆኑን እስኪ
ዘነጋና እስኪጠራጠር ደካማ ሆኖ ቀረበ። ዲያብሎስም ፍጡር መስሎት ነፍሱን በሲኦል፥ ሥጋውን በመቃ
ብር ሊቆራኝ በቀረበ ግዜ አምላክ በነፋስ አውታር በእሳት ዛንጀር ወጥሮያዘው። ዲያብሎስም መሸነፉን
አመነ፥ ከእርሱ በላቀ ጥበብ ክርስቶስ እንዳሸነፈው ተረዳ፥ ምርኮኞቹም ለዳግማዊው አዳም ለእየሱስ ክ
ርስቶስ አስረከበ።

### <u>የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት፤</u>

ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ የባሕርይ ልጅ ነው። በኋለኛው ዘመን ንጽሕት ቅድስት ከምትሆን ከድን
ግል ማርያም ተወለደ። ከሦስቱ አካል አንዱ አካል ወልድ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ፍጡር ሳይሆን ፈጣሪ ነው
፥ አማላጅ ሳይሆን ተማላጅ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ወልድ እኛን ለመፍጠር የተፈጠረ አይደለም፥ እ
ኛ በእሱ ተፈጠርን እንጂ፥ «በእሱ ኹሉ ተፈጠረ» ዮሐ.1፥3።

ለእኛ መፈጠርያ እንዲሆን ልዑሉና ኃያል እንደ አገልግሎት መሣሪያ ተፈጠረ ብሎ ማውራት
ከደካማ አስተሳሰብ የተገኘ ነው። ዓለምን እንደፈጠረ የታወቀ ቢሆንም፥ ወልድ ምንም ግዜ ነበረ፥ ያልነ
በረበት ጊዜ የለም። በእርግጥ ያለ እሱ ምንም አልተፈጠረም፥ ሁሉም በእርሱ የተፈጠሩ ናቸው። ያለ
እጅ ምንም መሥራት እንደማይቻል፥ ወልድምየአብ እጁ (ክንዱ) ነውና። አብ በወልድ ዓለማትን ፈጠረ
ሲባል በእጅ ጥልፍ እንደ መጥለፍ፥ ስዕል እንደመሳል ማለትነው።

አብ የወልድ አባት ነው እንጂ ፈጣሪ አይደለም። አባት ከሆነ ፈጣሪውም መሆን አለበት የሚ
ሉ አሉ፥ ተሳስተዋል። አባትና እናታችን የእኛ ወላጆች እንጂ ፈጣሪዎች አለመሆናቸው የታወቀ ነው።
አብን ከወልድ፥ ወልድን ከአብ ለያይተን መናገር አይቻለንም። ቅዱስ አትናቴዎስን አባባል እዚህ ላይ
እንጠቅስዋለን። የፀሐይ መኖር በጸዳሉ፥ የእሳት መኖር በነበልባሉ እንዲታወቅ አብን ያወቅነው በወልድ
ነው። ጸዳል ከብርሃኑ እንደማይለይ፥ ወልድ ከአብ፥ አብ
ከወልድ አይለይም። ፀሐይና ጸዳል ሁለት ፀሐዮች እንደማይባሉ አብና ወልድም ሁለት አማልክት አይባ
ሉም። ለዚህምማስረጃ «እኔ በአብ፥አብም በእኔ ነው» ብሏል። ዮሐ. 4፥10።

ከዚህ ተላልፈን እንደ አርዮስ ወይም አሁኖቹ የይሖዋ ምስርክሮች አብ ወልድን አጸናው ወይም ፈጠረው ማለት ሕይወት ሕይወትን አጸናው እንደማለት ነውና ወልድ ሕይወት ሊሆን አይችልም። ዮሐንስ 14፥6 «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ»

### ወልድ ሥጋን በመዋሃዱ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ አንሷልን?

በፍጹም! ሰውን ለማዳን ሲል ሰው የሆነው የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ወልድ ሰውም ቢሆን ከአምላክነቱ የጐደለበት የለም። ተለውጦ ሌላ አልሆነም፥ ያው እሱው ነው እንጂ። «ቃል ሥጋ ሆነ» የሚለውን በመጥቀስ ብዙዎች ራሱ ያ ቃል ወደ ሥጋነት ተለወጠ እንጂ ከማርያም ሥጋ አልወሰደም የሚሉ መናፍቃን አሉ። እግዚአብሔርም ግን በባሕርይው ሕልፈት ውላጤ የሌለበት ስለሆነ «እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም» ሚልክ.3፥6 በማለት በመለወጥ ሳይሆን በተዋሕዶ ሰው መሆኑን ያስረዳናል።

ስለሆነም ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ ልጅ የማርያም ልጅ ሲሆን፥ የነበረ፥ ያለና የሚኖር እንጂ ሰው ሆኖ በምድርሳለ ከአብ ዕሪና አልተለየም፥ ተለውጦም ፍጡር ወይም አማላጅ አልሆነም። «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናና ዛሬ እስከ ዘላለም ያው ነው» እብራውያን 13፥8።

በወንጌል የተመዘገበው ድካሙንም ኃይሉንም የገለጠበት ማንኛውም ድርጊት የራሱ የሥግው ቃል ነው። ከኃጢአት በቀር የሰው የሆነውን ሁሉ የራሱ አድርጓልና። ብዙ ድንቅ ድንቅ ተአምራትን ያደረገው እርሱ ተራበ ተጠማ፥ አዘነ፥ አለቀሰ። በጌቴሴማኒ የጸለየው በጐልጐታ መራራ ጩኸት ያሰማው፥ እሱ የዕለት ሬሳ ወልደ መበለትን ወለተ ኢያኤሮስን የአራት ቀን ሬሳ አልዛርን ያስነሳው ራሱ ሥግው ቃል ነው። ማቴ.9፥25 ሉቃ. 7፥11-16 ፤ ዮሐ.11፥34።

ይሁን እንጂ ወልድ በባሕሪው መዋቲነት (ሞት) የሚስማማው ነበር ማለት አይደለም፤ የክርስቶስ ሞት በሥጋ መሆኑን ሐዋርያው ጴጥሮስ ተናግሮታል። «ክርስቶስ በሥጋ ስለእኛ መከራን ስለተቀበለ...»1ኛ ጴጥ.4፥1። ስለዚህ የክርስቶስ መከራ መቀበል በመዋዕለ ሥጋዌ በተደረገው መግቦት ከሆነ እግዚአብሔር ሞተልን ብሎ መናገር አያስቸግርም፤ መለኮት በሥጋው ሞተ ይባላል እንጂ። የሥጋዌን ሥርዓት ዓለም ከመፍጠሩ በፊት ካለው ሁኔታ ጋር ቀላቅሎ እግዚአብሔርበባሕርይው ሞተ ብሎ መናገር አይገባም፥ ክህደትም ነው። ሦስቱ አካላት ሞቱ እንደማለት ነውና፥ እግዚአብሔርነት የሦስቱም አካለት ማለትም የአብ፥ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ገንዘብ ነው።

### የንስጥሮስ ትምህርት ስለኢየሱስ ክርስቶስ፤

ንስጥሮስ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው በ431 አ.ም. የተወገዘ መናፍቅ ነው። የንስጥሮስ ትምህርት በአጭር ሲገለጽ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት አካል ሁለት ባህርይ ነው፥ የማርያም ልጅ ሌላ፥ የአብ ልጅ ሌላ ነው ይላል። የማርያም ልጅ ለአብ ልጅ ማኅደሩ ሆነ፥ የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ አካላዊ ነው ይላል። ይህም ማለት ሥጋ ለቃል ማኅደሩ፥ ተሸካሚው፥ ልብሱ፥ መቅደሱ ነው ማለት ነው። እንደ ንስጥሮስ አባባል ሥጋና ቃል ዳዊትና ማኅደር፥ ሰይፍና ሰገባ መሆናቸው ነው ማለት ነው። ይህም ማለት ማኅደር ከመጽሐፍ መለየየት እንደሚችል ቃልና ሥጋም የተለያዩ ማለት ነው። ይህ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በቅዱሳን አባቶች የተወገዘ ነው። የክርስቶስ አንድ አካል መሆንን በኋላ እናያለን።

### የፓፓ ሊዮን ትምህርት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ

ፓፓ ሊዮንም ሆነ ተከታዮቹ ከንስጥሮሳዊ አስተሳሰብ ያልራቁ፥ ኢየሱስ ክርስቶስን አንድ አካል ሁለት ባሕርይ የሚሉ ናቸው። በሎጂክ (በመሠረተ እውነት) የንስጥሮስ አስተሳሰብ ከእነሱ ይልቅ እውነታነት አለው፤ ምክንያቱም አካል ያለባሕርይ፥ ባሕርይ ያለ አካል አይገለጥምና። ሁለት ባሕርይ ካሉ የግዴታ ሁለት አካል ማለት ነበረባቸው። እነሱ ግን አካልን አዋሕደው አንድ ካሉ በኋላ ባሕርዩን ከፋፈሉ። መለኮት የመለኮትነትን ሥራ ይሰራል፥ ሥጋ የሥጋን ሥራ ይሠራል ብለው ያምናሉ። ይሄም ከሐዋርያት ትምህርትና ከመጸሐፍ ቅዱስ ውጭ መሆኑን ቀጥለን እናየዋለን።

**የኢየሱስ ክርስቶስ ተዋሕዶ በቅዱሳን አባቶች ሲተነተን፤**

ቅዱስ ቄርሎስ ስለቃልና *ሥጋ* ተዋሕዶ እንዲህ ይላል። «ቃል *ሥጋ ሆነ* ሲባል ቃል ተለውጦ *ሥጋ ሆነ* ማለት አይደለም፤ *ሥጋም* ወደ አምላክነት ተለወጠ ማለት አይደለም።» በማይመረመር የተዋሕዶ ምስጢር የቃል ሀብት ለ*ሥጋ*፥ የ*ሥጋ* ሀብት ለቃል ሆነ እንጂ። ይህም ማለት የመለኮት ገንዘብ በተዋሕዶ የ*ሥጋ* ገንዘብ፥ የ*ሥጋ* ገንዘብ በተዋሕዶ የቃል ገንዘብ ሆነ ማለት ነው። ፊተኛና መጨረሻ መባል የሚገባው ቃል ሲሆን፥ *ሥጋ* ግን በተዋሕዶ የቃልን ገንዘብ የራሱአድርጓልና ፊተኛም መጨረሻም እኔ ነኝ ሊል በቃ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ነው። ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ እንዴት እንደሆነ አንመልከት።

<u>መለኮታዊ አካል</u>፥ ረቂቅ፥ የማይጨበጥ፥ የማይዳሰስ፥ እሳታዊ፥ ምሉዕ የሆነ።

<u>*ሥጋዊ* አካል፥</u> ግዙፍ፥ ውሱን፣ የሚዳሰስ፥ የሚጨበጥ።

<u>መለኮታዊ ባሕርይ፥</u> ፊተኛና ኋለኛ፥ የመጀመሪያና መጨረሻ፥ ፈጣሪነት፥ ሁሉን በነገር ማድረግ መቻል፥ ዘላለማዊነት፥ የማይሞት፥ የማይለወጥ፥ የማይታመም የማይራብ፥ የማይጠማ፥ የማይደክም።

<u>*ሥጋዊ* ባሕርይ ፥</u> መራብ፥ መጠማት፥ መድከም፥ መሞት የሚስማማው።

እንግዲህ ወልድ የአዳምን ልጅ ከሰይጣን ባርነት ሊያድነው ሲመጣ ቃል ከ*ሥጋ ጋር* ተዋሐደ ማለት መለኮታዊአካልና *ሥጋዊ* አካል ተዋሃዱ፤ መለኮታዊ ባሕርይና *ሥጋዊ* ባሕርይ ተዋሐዱ። ከእመቤታችን የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል፥ ባለመለወጥ በተዋሕዶ ማለት ነው መለኮት መለኮትነቱን ሳይለቅ፥ *ሥጋ ሥጋ*ነቱን ሳይለቅ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆነ። ለዚህም ነው ክርስቶስ ፍጽም አምላክ ፍጽም ሰው የሚባለው።

የ*ሥጋ*ና የመለኮትን ተዋሕዶ ቅዱስ ቄርሎስ በብረትና በእሳት መስሎ ይናገራል። ብረት ከእሳት ሲገባ ከእሳት ሲዋሐድ መጠኑን ቅርጹን ወርዱን ቁመቱን ሳይለቅ የእሳቱን ሀብት ወርሶ ሙሉ ሁለንተናው ፍጽም እሳት እንደሚሆን፥ እሳትም የእሳትነት ባሕርዩን ጠባዩን ሳይተው በብረቱ መጠን የብረቱን ቅርጽ እንደሚይዝ ኋላም አንጥረኛ በመዶሻ ሲያለዝበው በመ*ጋ*ዝ ሲተረትረው፥ በብረትና በእሳት መካከል ምንም ልዩነት እንደማይታይ መለወጥ ኅድረት የሌለበት የመለኮትና የ*ሥጋ* ተዋሕዶም እንደዚህ ነው። ስለዚህ አንዱ ክርስቶስን ከፍሎ *ሥጋ* የ*ሥጋ*ን *ሥራ* ይሠራል፥ መለኮት የመለኮትን *ሥራ* ይሠራል ማለት የተሳሳተ ትምህርት ነው።

## <u>*ሥጋ* በተዋሕዶ የባሕርይ አምላክ መሆኑን የሚያስረዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ፤</u>

<u>ትንቢተ ዳንኤል 7፥13</u> «በሌሊት ራዕይ አየሁ፥ እነሆም የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ዳመናት ጋር መጣ፥ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፥ ወደ ፊቱም አቀረቡት። ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትን ክብር መንግሥትም ተሰጠው። ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፥ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው»። ሥልጣንያለው፥ የአምላክነት ሥልጣን ማለት ነው። ይሄ የተነገረው ለመለኮት ብቻ ነው እንዳንል የሰው ልጅ ብሎ ገልጾልናል፥እንግዲህ ትስብእት (ስውነት) በተዋሕዶ አምላክ አይሆንም ከተባለ፥ ሕዝብና ነገደ ልሳናት ያመልኩታል ተብሎ እንዴትተጻፈለት?

<u>መዝሙር 2፥7</u> «እግዚአብሔርም አለኝ፥ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ» እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ አንድ ልጁን ከእመቤታችን የሚዋሐደውን *ሥጋ* በአካል፥ በባሕርይ፥ በፈቃድ አንድ እንደሆነ አስቀድሞ ያውቃልና እኛን ለማስረዳት ዛሬ ወለድኩህ ብሎ መስከረለት።

**መዝሙር** 47፥5 «እግዚአብሔር በመለከት ድምጽ ዐረገ፥ ዘምሩ ለአምላካችን ዘምሩ ዘምሩ ለንጉሣችን ዘምሩ» ሐዋርያትሲያርግ ያዩት አምላክ የሆነ ሰውን መሆኑን ዳዊት ገለጸልን። ያለበለዚያማ እግዚአብሔር ብሎ ባልጠራው ነበር።

**ዮሐንስ ወንጌል** 9፥35 «..አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን? አለው እርሱም መልሶ ጌታ ሆይ በእርሱ አምን ዘንድ ማን ነው? አለ።ኢየሱስም አይተኸዋልም፥ ከአንተ ጋርም የሚናገረው እርሱ ነው አለው » ባለቤቱ ራሱ በተዋሕዶ የለበሰው ሥጋ አምላክ እንደሆነ ያውቃልና በደረቅ ግንባር ዓይን ለፈጠረለት ዕውር የእግዚአብሔር ልጅ ማነው አምንበት ዘንድ ቢለው ያየኸው ካንተ ጋር የሚነጋገረው እርሱ ነው ብሎ መሰከረ እንጂ በእርሱ ውስጥ ያለው አላለም። የአብ ልጅየማርያም ልጅ ነውና።

**ዮሐንስ ወንጌል** 1፥14 አንድ ልጅ አንድ ክብር አንድ ገጽ አንድ ሥራ አየን ብሎ እያስተማረ! በተዋህዶ አንድ ለሆነ ትስብእት አንድ ልጅ፥ አንድ ገጽ፣ አንድ ክብር አየሁ ብሎ መሰከረ። ጴጥሮስም «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» ብሎ መለሰ። አንተ ያለው በተዋህዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆኖ በፊቱ ተቀምጦ የነበረው ጌታችን ኢየሱስን አይደለም? ማቴ.16፥16።

**ኢሳይያስ** 9፥6 «ሕፃን ተወልዶልናል፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፥ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፥ ስሙም ድንቅመካር ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» ሕፃኑን ጌታን የዘላለም አባት፥ ብርቱ አምላክ፥ የሰላም አለቃ ነው ያለው ሥጋ ተዋሕዶ ከቃል ጋር አንድ ሆኗልና መለኮትና ትስብእት በባሕርይ ተዋሕዶ አንድ ከሆኑ በኃላ አንኳን በግብር በሐሳብ መለየት አይገባም።

**ዕብራውያን** 5፥7 ቅዱስ ጳውሎስ ቃል ሥጋ በተዋሐደ ጊዜ አለቀሰ ጸለየ አለው። ማልቀስ መጸለይ መፍራት ለሥጋ ነውእንጂ ለመለኮት አይደለም። ዳሩ ግን ለመለኮትና ሥጋ በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ ስለሆኑ ሥጋ የሚሠራውን መለኮት፥ መለኮት የሚሠራውን ሥጋ ይሠራል።

**ዮሐንስ ራዕይ** 1፥17 «..አትፍራ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥ ሞቼም ነበርኩ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ» ሥጋ በፊትና በኋላም መሆን አይሆንለትም። ቅድመ ዓለም ድኅረ ዓለም የሚኖር አምላክ ብቻ ነው።ሞትም የሥጋ ነው እንጂ የአምላክ አያደለም። ባለቤቱ ግን ከሥጋ ጋር አንድባህርይ መሆኑን ያውቃልና የፊተኛውም የኋለኛውም የሞትኩትም እኔ ነኝ ብሎ ተናገረ።

**ዮሐንስ ወንጌል** 6፥51 «ከስማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ» ከስማይ የወረደ እንጀራ ማለቱ ከእመቤታችን የነሣውን ሥጋ አይደለምን? ወይስ ከስማይ ሥጋውን ይዞት ወረደ ሊባል ነው? ይህ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጻፈም። ከስማይ የወረደው ቃል ብቻውን ነው፥ ግና በባሕርይ ተዋሕዶ ሳይቀላቀል ሳይደባለቅ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ እንላለን። ያለዚያማ ከስማይ የወረድኩ እንጀራ እኔ ነኝ አይልም ነበር።

## የኢየሱስ ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆን በመጽሐፍ ቅዱስ

1ኛ **ዮሐ. መልእክት** 1፥1 «ከመጀመሪያ ጀምሮ ነበር ያለው ማንን ነው? ቀዳማዊ ቃል መለኮት አይደል? በሥጋ ዐይን እንዴት ይታያል? እጅስ እንዴት ትዳስሰዋለች? ቃል ከሥጋ ጋር በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ ካልሆነ በቀር ቅድመ ዓለም የነበረውን መለኮት እንዴት አየነው ዳሰስነው አለ? የሚታይ የሚዳሰስ ግዙፍ የሆነ እንጂ ረቂቅ የሆነ እንዴት ይታያል? እንዴትስ ይዳሰሳል? ቃል ከሥጋ ጋር በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ካልሆነ?።

**<u>የሐዋ. ሥራ 20፥28</u>** «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን» እግዚአብሔር ረቂቅ መንፈስ ነው፥ ደምም የለው። ደም የሥጋ ነው፥ ዳሩ ግን መለኮትና ትስብእት በማይለይ ተዋሕዶ አንድ ባሕርይ፥ አንድ አካል ስለሆነ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ እርሱ በደሙ የዋጃትን አለ። ኢየሱስ በደሙ የዋጃትን ቢል እንኳን ሁለት ባሕርይ ባዮች መግቢያ ባገኙ ነበር። የትስብእት ስም ነውና ብለው፤ አሁን ግን ለይቶ እግዚአብሔር ብሎ ነው የጠራው። እንግዲህ ምን ይበሉ?

**<u>ማርቆስ 14፥61</u>** «የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን? አለው። ኢየሱስም እኔ ነኝ የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ዳመና ሲመጣ ታያላችሁ አለ» ቀያፋ በጉባኤ መካከል የጠየቀው የተያዘውን ኢየሱስን አይደለምን? ሁለት ባሕርይ ነው ካሉ በማናቸው ባሕርይ ነኝ አለ? በመለኮት ባሕርይ ነው እንዳይሉ መለኮት ግዙፍ አይደለ አይያዝ፥ አይታሰር። ያልተያዘ ያልተጠየቀ እንዴት እኔ ነኝ ብሎ መሰከረ? ተይዞ የተጠየቀው የሥጋ ባሕርይ ብቻ ነው ቢሉ የእግዚአሔር የባሕርይ ልጁ እኔ ነኝ ብሎ እንዴት በሐሰት ይመሰክራል? እንደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት በተዋህዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ካልሆነ በቀር የዚህን ምስጢር ማንም በትክክሉ ሊመልስ አይችልም።

**<u>ማርቆስ 15፥37</u>** «የመቶ አለቃ እንደዚህ ጮሆ ነፍሱን እንደ ሰጠ ባየ ጊዜ፥ ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበር አለ። እየው! ተገርፎ ከመስቀል ላይ የተቸነከረውን የማርያም ልጅ መድኃኔዓለም ክርስቶስን የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ እንደሆነ ሲያስረዳ?።

**<u>መዝሙር 21 (22)፥12-18</u>** «ልቤ እንደ ሰም ሆነ.... እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ» አየኸው? ቃል በተዋሕዶ ለሥጋ የሆነውን ሁሉ ለራሱ ሲያደርግ? ከመስቀል ላይ የተቸነከረው ሥጋ ሲሆን ከሺህ ዘመን አስቀድሞ ቀዳማዊ ቃል በዳዊት አድሮ አንድ ባሕርይ መሆኑን ሲያስረዳን?።

**<u>ዮሐንስ ራዕይ 2፥8</u>** «ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል......» ቅድመ ዓለም የነበረ ድኅረ ዓለም የሚኖር እግዚአብሔር ብቻ ነው እንጂ ለሰው አይቻለውም። እግዚአብሔር እንዳይሞት እናውቃለን፥ ባለቤቱ ግን ሙቼ ነበርኩ እነሆም ሕያው ነኝ አለ። በሰውነቴ ባሕርይ ሙቼ ነበርኩ እነሆም ሕያው ነኝ አለ። በሰውነቴ ባሕርይ ሙቼ ነበርኩ አላለም። መለኮት በሥጋው ሞተ እንጂ። እንግዲህ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ካልሆነ በቀር ቅድመ ዓለም የነበረና ሞቶ የተነሣ መሆኑን ባልገለጸ ነበር። ቅድመ ዓለም የነበረው አንዱ እሱ ነው፥ ሙቼም ነበር ያለው ቅድመ ዓለም የነበረው ድኅረ ዓለም ዓለምን አሳልፎ የሚኖር የሞተው ሌላ አይደለም፥ ሥጋ የሆነ ቃል እንጂ።

**<u>ፊልጵስዮስ 2፥6</u>** «በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ እግዚአብሔርነትን እንደመቀማት አልቆጠረውም፥ የባሪያን መልክ ይዞ መጣ» አየህ ቅዱስ ጳውሎስ አዋሕዶ አምላክ ስለሆነ በእግዚአብሔር መልክ ነበር አለ።

**<u>ሮሜ 5፥10</u>** «ጠላቶቹ ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን....» በመስቀል ላይ የተሰቀለው ኢየሱስ የማርያምልጅ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ነው ብሎ መሰከረ። የማርያም ልጅ ሌላ፥ የአብ ልጅ ሌላ ቢሆን ኖሮ ወይም የተሰቀለው ሥጋዊ ባሕርይ ብቻ ቢሆን ኖሮ በልጁ ሞት... ባልተባለ ነበር። ቅዱስ ጳውሎስ ግን መክፈል በሌለበትና አንድ በሆነው በእሱ ላይ የማይገባ ፀያፍ ነገር መናገር እንደማይገባ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑን መሰከረ።

**<u>ማቴዎስ 3፥17</u>** «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ» እንግዲህ ራሱ አብ ከእመቤታችን የተወለደውን መድኃኒታችን ኢየሱስ ልጄ ነው ሲል። በኢየሱስ ውስጥ አድሮ ያለው ቢል ኖሮ ንስጥሮ ሳውያውን መግቢያ ባገኙ ነበር።አብ ግን ሥጋና መለኮትን አንድ አድርጎ አዋሕዶ ነው የምወደው ልጄ ብሎ የመሰከረው። ታዲያ የማርያም ልጅ ሌላ፥ የአብ ልጅ ሌላ ነው የሚል ትምህርት ከየት መጣ? ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት

በማድረግ ነው ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ ልደት ከበረ፥ ከሁለት አካል አንድ አካል፥ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባህርይ ሆነ የምትለው።

<u>ዮሐንስ ወንጌል 15፥24</u> «አሁን ግን እኔንም አባቴንም አይተውማል ጠልተውማል» አይሁድ ያዩት ሥጋ ነው፥ ረቂቁን መለኮት አላዩም።ባለቤቱ ግን ስንኳን እኔን አባቴን አይተው ጠሉ አለ። ሥጋ ከቃል ጋር በባሕርይ ተዋሕዶ አንድ ስለሆነ እኔን ያየ አብን ፈጸሞ አየ፥ እኔን የጠላ አብን ፈጽሞ ጠላ አለ። አ ለዚያ አንድ ባሕርይ አንልም ካሉ አይሁድ ያዩት ሥጋን ነው እንጂ ቀዳማዊ ቃልን አላዩም። አንግዲህ ለምን ተኮነኑ ይላቸዋል? ባላዩ እንዴት ይኮነናሉ፥ ጌታስ ሳያዩት አይተው ጠሉኝ እንዴት አለ? በተዋሕ ዶ አንድ ባሕርይ ካልሆነ በቀር?።

<u>ዮሐንስ ወንጌል 17፥24</u> «አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር ስለወደድከኝ ክብሬን እንዲያዩ....» የተናገረው ኢየ ሱስ ነው። ስለራሱ ተናገረ እንጂ ስለ ሌላ አልተናገረም። ከቀዳማዊ ቃል ጋር በባሕርይ በፈቃድ አንድ ካልሆነ በቀር እንዴት አብን ደፈረና ዓለም ሳይፈጠር ወደኸኛል አለው? ሳይኖርስ ወደደውና ነው? ያልኖ ረስ እንዴት ይወደዳል? ወይስ ሳይኖር ኖርኩ አለ?

<u>ዮሐንስ ወንጌል 3፥14</u> «ሙሴ በምድረ በደ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለ ም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል» በመስቀል ላይ የተሰቀ ለውን ኢየሱስን የሥጋ ባሕርይ ነው የሚሉት ከእግዚአብሔር ከባሕርይ ልጁ ጋር በባሕርይ በፈቃድ አን ድ ካልሆነ እንዴት በርሱ የሚያምን ሁሉ አይጠፋም የዘለዓለም ሕይወት ትሆንለታለች ይላል? የሰው ደ ም ከኃጢአት ያነጻልን? በፍጹም! ልዑል እግዚአብሔር በትንቢተኤርምያስ ምዕ 17፥15 ላይ «በሰው የሚ ታመን ሰው ርጉም ነው» ይላል።

<u>ዮሐንስ ወንጌል 3፥16</u> «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግ ዚአብሔር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲህ ወዶአልና» በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ደሙን አ ፍስሶ ሥጋውን ቆርሶ የሰውን ልጅ በደሙ የዋጀው የማርያም ልጅ ኢየሱስ አይደለምን? ከቃል ጋር በተ ዋሕዶ አንድ ልጅ አንድ ባሕርይ ካልሆነ አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረሰ አለም አለ?

<u>ዮሐንስ ራዕይ 5፥12</u> «የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት፥ ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከት ም ሊቀበል ይገባዋል» የታረደው በግ የተባለ ከእኛ ሥጋና ደም የሆነ ሰው ነው። ከንጽህት ቅድስት ድን ግል ማርያም በሕቱም ድንግልና ተፀንሶ በሕቱም ድንግልና የተወለደው ነው ቅድመ ዓለም ካለውና ከነበረ ው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በተዋህዶ አንድ አካል አንድ ባህርይ ካልሆነ ይህ ሁሉ ክብርና ልዕልና እን ዴት ተሰጠው? ትስብእት በተዋህዶ ከቃል ጋር አንድ ባህርይ ካልሆነ እንዴት ይህ ሁሉ ልዕልና (ለመለኮ ት ብቻ የሚቀርብ) ምስጋና ቀረበለት? እስከ አሁን የዘረዘርናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የክርስቶስን አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆን የሚያረጋግጡ ናቸው።

<u>ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው</u>

የይሖዋ ምስክሮች፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ስም ሊጠራ አይገባውም እርሱ ሁሉን የሚችል አምላክ አይደለም እንዲያውም ኢየሱስ ክርስቶስ ሚካኤል የሚባለው የመጀመሪያ መልአክ ነው ይላሉ። ኢየሱስ ክርስቶስግን የመላእክት ፈጣሪ «መላእክቱን መናፍሰት አገልጋዩቹንም የእሳት ነበል ባል የሚያደርግ» ሁሉን ቻይ ፈጣሪ ነው። ዕብ 1፥7 መልአክ አለመሆኑንም ጳውሎስ ሲናገር «ከመላእ ክትስ አንተ ልጄ ነህ ዛሬ ወልጄሃለሁ» ያለው ከቶ ማን ነው?በማለት ክርስቶስ መልአክ አለመሆኑን ያስ ረዳል። የክርስቶስን እግዚአብሔርነት መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ያቀርባል።

<u>ኢሳይያስ 45፥20-24</u> «...ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም እኔ ድንቅ አምላክና <u>መድኃኒት ነኝ</u> ከእኔም በቀ ር ማንም የለም እናንተ የምድር ዳርቻ ሁሉ እኔ አምላክ ነኝና ከእኔም በቀር ሌላ የለምና ወደ እኔ ዘወ ር በሉ ትድኑማላችሁ» በዚህ ቦታ ላይ እግዚአብሔር ከእርሱ ሌላ አምላክ እንደ ሌለ መድኃኒትም እ ሱ መሆኑን ገልጾአል። ይህን የመሰለ ሌላም ጥቅስ እንጨምር።

ትን. ሆሴእ 13፥4 «እኔ ግን ከግብጽ ምድር ጀምሬ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም በቀር ሌላ መድኃኒት የለም፥ ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ አታውቅም» አሁንም ከእሱ ከእግዚአብሔር በስተቀር አምላክና መድኃኒት እንደሌለ በማይታበል ቃሉ ነግሮናል። አሁንም ሌላ ይህን የመሰለ እንጥቀስ።

ቲቶ 1፥3 «መድኃኒታችን እግዚአብሔር እንዳዘዘ» እንግዲህ ከላይ እንደተጠቀሰው ለሰው ሁሉ መድኃኒት ሊሆን የሚችል እግዚአብሔር ብቻ መሆኑ ተገልጿል፣ የሚከተሉትን ጥቅሶች ከላይኛዎቹ ጋር እናነጻጽራቸው።

ቲቶ 2፥12-13 «የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁንና የአምላካችንን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ» ለጌታችን ክብር ምስጋና ይግባውን፥ ጳውሎስ ለቲቶ የክርስቶስን አምላክነትና መድኃኒትነት ገለጸለት። እንግዲህ ክርስቶስ ፍጡር ከሆነና እግዚአብሔር ካልሆነ እንዴት አምላክ መድኃኒት ሊባል ቻለ? እግዚአብሔር ከሆሴዕ «እኔ ብቻ አምላክና መድኃኒት ነኝ» ብሏል፥ የባሕርይ አምላክ እርሱ ብቻ ነውና። ጻድቃን አማልክት ቢባሉም በጸጋ ነው፥ የክርስቶስ አምላክነት ግን የባሕርይ ነው።

የሐዋ. ስራ 4፥12 « መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና»

ሉቃስ 2፥11 «ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋል።»

ዮሐንስ ወን. 4፥42 «... እርሱም በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ እናውቃለን» የኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒትነቱ ከታመነ እግዚአብሔር መሆኑ መታመኑ ግዴታ ነው። ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ሌላ መድኃኒት የለምና ያ በዘመነ ብሉይ ከእኔ በቀር አምላክ መድኃኒት የለም ያለው እግዚአብሔር በኋለኛው ዘመን ንጽሕት ከምትሆን ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ተወለደ አምላክ ሰው ሆነ። ሌሎች ማስረጃዎችም እናቅርብ፥

ኢሳ. 9፥6 «ሕጻን ተወልዶልናል፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፥ ስሙም ድንቅ መካርኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ፥ እነኝህ ኃይለ ቃላት ለእግዚአብሔር ብቻ የሚነገሩ ናቸው። ጌታም እግዚአብሔር ስለሆነ ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባትየሰላም አለቃ ተባለ። ይህንንም በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ማስረዳት ይቻላል። «ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን?አንድ አምላክስ የፈጠረን አይደለምን?» ሚልክያስ 2፥10 አዎን ሥላሴ በባሕርይ በአገዛዝ በመፍጠር አንድ ስለሆኑ አንድ አምላክ ፈጠረን ይባላል። ጌታ የዘለዓለም አባት ከሆነ ሚልክያስ የመሰከረለት አንዱ አባታችን እርሱ ነው።

ዮሐንስ ራዕይ 1፥8 «ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ ይላል»፥ «እግዚአብሔር ሙሴን ያለና የሚኖር እኔ ነኝ አለው» ዘፀአት 3፥14፥ በዮሐንስ ራዕይ ላይ የተጠቀሰው ለጌታ ነው ያለውንየነበረው እግዚአብሔር መሆኑ በዘፀ 3፥14 ላይ ደግሞ የተጠቀሰ ነው። እንግዲህ ይሖዋ ማለት ክርስቶስ ነው። ምክንያቱም ይሖዋ ማለት ያለ የነበረ የሚኖር ማለት ነውና።

የዮሐ. ራዕይ 22፥12 «እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእየአንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ኦሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ» ይህን ያለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይህን ከኢሳይያስ የምስክርነት ቃል ጋር እናዛምዳው «እነሆ ጌታ እግዚአብሔር እንደ ኃይል ይመጣል፥ ክንዱም ስለእርሱ ይገዛል እነሆ ዋጋው ከእርሱ ጋር ደመወዙ በፊቱነው» ኢሳ 40፥10 ለፍርድ የሚመጣው ክርስቶስ ኢየሱስ መሆኑበመጽሐፍ ቅዱስ የሰፈረ ነው። ኢሳይያስ ጌታን እግዚአብሔር ብሎ እንደጠራው ልብ አልክ? ጌታም ዋጋ ሰጪ መሆኑን ተናግሯል። ኢሳይያስም ዋጋው ከእርሱ ጋር ነው ብሎ ተናገረ።

**የሐዋ. ሥራ 1፥9** «ይህንንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው» ሐዋርያት እያዩት በመርቀቅ ሳይሆን በመራቅ ያረገው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ዳዊት እንዲህ ብሏል «አምላክ በእልልታ እግዚአብሔር በመለኮት ድምጽ  ዐረገ» መዝ 46(47)፥5። እንግዲህ ያረገው አብ አይደለም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ ታዲያ እግዚአብሔር ካልሆነ ዳዊት እግዚአብሔር ብሎ ለምን ጠራው?

**የሐዋ. ሥራ 1፥11** « የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችሁ? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁም ይመጣል» መጪው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን መላእክትም መስክረዋል። ዳዊት ደግሞ «ከክብሩ ውበት ከጽዮን እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል» መዝ 49(50)፥2 ብሎ የሚመጣው ኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔር ብሎ ጠራው። መቸ በዳዊት ብቻ ይቆማል፥ ዘካርያስም «አምላኬ እግዚአብሔር ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ይመጣል» ትን. ዘካ 14፥5 ብሎ ክርስቶስን እግዚአብሔር ብሎ ጠርቶታል። ጳውሎስ ደግሞ የዘካርያስን ምስክርነት ይዞ «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶሰ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ሲመጣ» 1ኛ ተሰሎንቄ 3፥12 ብሎ መስክሯል።

የአምላክን ሰው መሆን በሚገባ ያልተረዱ ብዙዎች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በፍጡር ደረጃና በትንሽ አምላክነት ሲላቸው ከአብ አሳንሰው በአማላጅነት ሲጠሩት ይሰማሉ። ለዚሁም ሰይጣናዊ ትምህርታቸው መጽሐፍ ቅዱስን ዋቢአድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹን ጥቅሶቻቸውን አውጥተናቸው ለስሕተታዊ ትርጉማቸውም ኦርቶዶክሳዊ የሆነ ምላሽ ተሰጥቶአቸዋል።

1/ **ማቴ 12፥32** «በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ በደሉ ይቅር ይባልለታል በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ ግን በዚህ አለምም ሆነ በሚመጣው በደሉ ይቅር አይባልለትም»

**መልስ፦** መናፍቃን እንደሚሉት ጌታን የሰደበ በበደሉ ይቅር ይባልለታል፥ አብና መንፈስ ቅዱስን ግን የሰደበ ለዘለዓለም እዳ ፍዳ ይሆንበታል ለማለትና ጌታን ዝቅ ለማድረግ አይደለም። በሰው ልጅ ላይ የስድብን ቃል የሚናገር ሁሉ በደሉ ይቅር ይባልለታል ማለቱ ተሳዳቢው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ሳይረዳ ባለማወቅሩቅ ብሲእ (ፍጡር) ተራ ሰው ብሎ ቢናገርና በኋላ የጌታን የባሕርይ አምላክነት ተረድቶ ቢጸጸት ለኃጥአቱ ስርየት ይኖረዋል። ምክንያቱም ጌታ ስውን ለማዳን ሲል ባሕርዩን ዝቅ አድርጐ በትሕትና ሰው የሚሠራውን ሥራ ከኃጢአት በስተቀር ሠርቷልና ለተሳዳቢው ምክንያት ይኖረዋል። ነገር ግን በሥጋ እግዚአብሔር እንደመጣ መምህራን ነግረውት፥ ወንጌል አንብቦ እየተረዳ ጌታን ፍጡር ወይም አማላጅ ቢል፥ ኃጥያቱ በዚህች ምድር ሆነ በኃይኛው አይስረይለትም ማለት ነው። ምክንያቱም በባሕርይ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸው።

2./ **ማቴ. 27፥46** «አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ»

**መልስ፦** ጥሬ ቃሉን ብቻ በመመልከት ብዙዎች በዚህ ቃል ሊሰናከሉ ይችላሉ። ዳሩ ግን ቃሉ ለተዋሕዶ ልጆች የሚያስናክል አይደለም። «ከኃይለኛው ሰው ቤት ገብቶ ገንዘቡን የሚዘርፍ ሰው አስቀድሞ እጁን ይዞ ካሰረ በኋላ ከቤት ገብቶገንዘቡን ይዘርፋል እንጂ አስቀድሞ እጁን ካላያዘውና ካላሰረው ከቤቱ ሊገባና ሊዘርፍ አይችልም» ብሎ ጌታ በማቴዎስ12፥29 በተናገረው መሠረት ዲያብሎስን አስሮ ሲኦልን ሊበረብር ባለ ጊዜ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ «አምላኬ አምላኬ ለማን ተውከኝ» የሚል ቃል አሰማው። ዲያብሎስም ይህን ሲናገር በሰማ ጊዜ ዕሩቅ ብእሲ (ፍጡር) መስሎት በሌሎች እንደለመደው (ከዚህ በፊት ሰይጣን ነፍስን ከሥጋ ይለይ ነበር) ነፍሱን ሥጋውን ለይቶ ሥጋውን በመቃብር ነፍሱን በሲኦል ሊቆራኝ ቀረበ። በዚህ ጊዜ ጌታ ምስጢረ መለኮቱን ብልጭ ቢያደርግለት መላእክት በመስቀል ዙሪያ ወድቀው «ለከ ኃይል ለከ ጸንዕ» ትርጓሜው ኃይል ይገባል፥ ጽንዕ ይገባል፥ እያሉ ሲያመስግኑት አይቶ ፈራ ደነገጠ። ከዚያም ሾልኬ አመልጣለሁ ብሎ ቢቃጣ በነፋስ አውታር በእሳት ዛንጀር አስረው። በዚህ ጊዜ እንዲህ ሲል ቀባጠረ። «ስውሆኖ ሥጋ ለብሶ ድል የነሳኝ ምእመናንን የነጠቀኝ ይህ ማነው? እንደ ኃጢአተኛ በመስቀል ተሰቅሎ ያለ ኃጢአት ሞቶ የወደድኩትን እንዳላደርግ

የከለከለኝ፥ ልቀርበው የማይቻለኝ ይህ ማነው? የተጠኝን ነፍሳት ሁሉ ወደ ክብር ወደ ልዕልና ይወስዳል እንጂ በእግሬ በእርግጥ በእጄ ጭብጥ አድርጌ ይዣቸው በነበረ ነፍሳት ላይ እንዳልስለጥን ያደረገኝ ይህ ማነው? ለካስ እኔ ሳላውቀው ነው እንጂ እሱስ ሰማያዊ ኖሯልና። ወይኔ ጠፋሁ በለልኩ ከእንግዲህ ወዲህ በእርሱ ካመኑ ሰዎች በማንማ ላይ ክፉ ማድረግ አይቻለኝም፥ ማንንም ለመጉዳት ሥልጣን የለኝም» ብሎ ፈጽሞ ድል መሆኑን መሰከረ። ከዚህ በኋላ ጌታ ነብያት የተናገሩትን ነገር እኔም ሰው የሆንሁባት ምስጢር እንዲህ ዲያብሎስን ለማስር ነው ሲልእነሆ ሁሉ ተፈጸመ ብሎ ክብርት ነፍሱን ከክብርት ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ ለየ (ዮሐ. 19፥30-31) በአካለ ነፍስም ከአዳም እሰከ እርሱ ድረስ ያሉት ነፍሳት ታስረው ተግዘው ወደ ነበሩበት ወደ ሲኦል ወረደ፥ ግእዛንን (ነጻነትን) ሰበከላቸው፥ ከቁራኛነት አስለቀቃቸው፥ ወደ ቀድሞ ቦታቸው ወደ ገነት መለሳቸው ፥1ኛ ጴጥሮስ 3፥20። ይህንን ያደረገበት ምክንያትስይጣን አዳምና ሔዋንን ያሳሳታቸው በእባብ ሥጋ ተሰውሮ (እባብን መስሎ) ነበር። ጌታ ደግሞ የስይጣን ብልሃት በብርቱ ሲሽር የሰውን ሥጋ ተዋህዶ ፍጹም ደካማ መስሎ ነው።

3/ <u>**ዕብ.** 5፥7</u> **«እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸት ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ»**

**መልስ፦** እግዚአብሔር ሰው የሆነበት ጠቅላላ አስተያየት በምክረ ስይጣን ተታሎ በኃጢአት ተጐሣቁሎ ኃይሉ ደካማ ጸሎቱ የማይሰማ ሆኖ ተፈርዶበት በመንፀፈ ደይን ወድቆ በእግረ አጋንንት ተጠቅጥቆ የነበረ የአዳምን ሥጋ ለብሶ በበደለው በደል ሁሉ እሱ ካሣ ሆኖ የረከሰውን ቀድሶ ያረጀውን አድሶ የቀደመ ልጅነቱንና ኃይሉን መልሶ ጸሎቱን ተሰሚ መስዋእቱን ጉዳይ ፈጻሚ አድርጎ ተዋግቶ ድል እንዲነሳና እንዲፈረድለት አደረገው፤ ከማሕበረ መላእክት ጨመረው ማለት እንጂ መናፍቃን እንደሚሉት ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ ከትንሣኤውም በኋላ እንደ ቅዱሳን ማማለድ የለበትም። ተሰሚነት ያጣውን የአዳምን ጸሎት ተሰሚነት እንዲኖረው ለማድረግ ብቻ ነው። በክርስቶስ ካሣ ይህን ሁሉ ሥልጣን ካገኘ በኋላ ያ ተዋርዶ በመንፀፈ ደይን ወድቆ ጽድቃችን እንደመርገም ጨርቅ ሆነ ይል የነበረው ሰው ጸሎቱ ተሰሚ መሥዋእቱ ጉዳይ ፈጻሚ ስለሆነለት «እኛ በክርስቶስ ፋንታ ክርስቶስን መስለን እንደ ክርስቶስ እንለምናለን፥ እግዚአብሔርም በእኛ ሰብከት ልጅነትን በእኛ ጸሎት ተድላ መንግሥተ ሰማይን ይሰጣችኋል» ለማለት በቃ 2ኛ ቆሮ 5፥20 በክርስቶስ አምሳል እንፀልያለን ብሎ በቃል የተናገረውን በገቢር ሲገልጽው ጌታ የ38 ዘመን በሽተኛ የነበረውን መጻጉዕ «ተነሳ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ» ብሎ እንደፈወሰው ዮሐ. 5፣8 ጴስሮስም ዮሐንስም ከእናቱ ማኅፀን ልምሾ ሆኖ ተወልዶ በመከራ ሥጋ ወድቆ ምጽዋት ሲለምን ይኖር የነበረውን ሰው «ወርቅና ብር የለኝም ያለኝንስ ልስጥህ እነሆ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነስተህ ሂድ» ብሎ አስነስቶታል የሐዋ. ሥራ 3፥1-12 ጌታ አልአዛርን እንደ አስነሳ ዮሐ.11፥41-45 ጴጥርስም ጸሎቱን ለእግዚአብሔር አቅርቦ «ጣቢታ ተነሽ» ብሎ የሞተችቱን አስነሳ የሐዋ. ስራ 9፥36-41 ክርስቶስ በመስቀል ለሰቀሉት ለአይሁድ «አባቴ ባለማወቅ ይሠሩታልና ይቅር በላቸው» ብሎ እንደጸለየላቸው ሉቃስ 23፥34 ከሐዋርያትም አንዱ እስጢፋኖስ በደንጊያው ከሚወግሩት ሰዎች «አቤቱ ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው ዕዳ በደል አትበልባቸው ብሎ ጸለየላቸው» የሐዋ. ሥራ 7፥60።

4/ <u>**ማቴ.**24፥36</u> **«ስለዚያች ቀንና ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም»**

**መልስ፦** ይህን በመጥቀስ ጌታ የሚመጣበትን ቀን አያውቅም ሰለዚህ ሁሉን የሚያውቅ ሁሉን የሚችል አምላክ አይደለም የሚሉ መናፍቃን አሉ። ነገር ግን ዮሐንስ በራእይ 1፥8 «ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ በማለት ሁሉን የሚችል ከእሱ በላይ ማንማ የሌለ መሆኑን ይናገራል። በተጨማሪም ጌታ በማቴዎስ 24፥1-55 ባለውላይ የምጽአቱን ዋዜማ እንዴት እንደሆነ ግልጽ አድርጎ ተናግሯል። ከእዚህ የምንረዳው ቢኖር የሚመጣበትን ቀን ማወቁን ነው። ታዲያ ስለምን ልጅም ቢሆን አያውቅም አለ?

**ሀ. ቀኒቱን ከአዳም ልጆችና ከመላእክት ሲለያት ነው እንጂ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱሰ ሲለይ አይደለም ፥ የሰው ልጅ ብሎ የአዳምን ልጆች ይጠራል።**

ለ. እንዲሁም ወልድ ቅድመ ተዋሕዶ አላዋቂ የነበረ ሥጋን እንደ ተዋሐደ ለማስረዳት በእውነት ጌታ የ ሰውን ባሕርይ ባሕርይው ማድረጉን ሊያስረዳን ፈልጐ ነው። እንዲህ ሲባል ከተዋሕዶ በኋላ ሥጋ አለአ ዋቂ ነው ማለት አይደለም። ከመለኮት ጋር አንድ አካል፥ አንድ ባሕርይ ከመሆኑ በፊት ያለውን ሲናገ ር ነው እንጂ።

ሐ. አንድም አብ ለልጁ በመስጠት አውቋታል ወልድ ግን በሥራ አላወቃትም፥ ይህም ማለት ጊዜው እስ ኪደርስ በልቤ አኖራታለሁ፥ በኋላ ግን በቃልነቴ እናግራታለሁ ሲል ነው። አብ ልብ፥ ወልድ ቃል፥ መን ፈስ ቅዱስ ሕይወት ነውና፥ በቃልነቱ በሥራ የሚገልጽበትን ሲናገር ነው።
መ. አንድም ወልድ ብቻ ያለ አብ አያውቃትም ሲል ነው። ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ አ ያውቃትም በባሕርይ በማወቅ አንድ ናቸውና። ንባቡ «ወልድም ቢሆን ያለ አብ ብቻውን» ስለሚል ነው ።

5. <u>**ዮሐንስ ወንጌል**</u> <u>14፥28</u> «ከእኔ አብ ይበልጣል» ይህንን ጥቅስ በመጥቀስ አብ ከወልድ ይበልጣል የሚ ሉ አሉ። ምስጢሩ ግን የሚከተለው ነው፥ ወልድ በተለየ አካሉ ሥጋን በመዋሃዱ መከራን የሚቀበል መ ሆኑን ሲገልጽ ነው። በዚህም ወልድ (ኢየሱስ ክርስቶስ) መከራውን ሁሉ ስለ ሰው ልጅ ፍቅር ሲል ተቀበ ለ። የማይሞተው ሞተ፥ ሰውን ከወደቀበት ለማንሳት ከጉስቁልናው ለማጣውት ወደ ቀድሞ ክብሩ ለመ መለስ ልዑል ባሕርይ አምላክ ራሱን አዋርዶ ሥጋን ተዋሕዶመከራን ተቀበለ። ይህንንም ሲያደርግ ብርሃ ነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ይኸውም የእግዚአብሔር መልኩ ነው፥ ቀምቶ እግዚአብሔር የ ሆነ አይደለም፥ ራሱን ዝቅ አድርጎ የአዳምን ባሕርይ ገንዘብ አደረገ እንጂ ሰውንም መሰለ። ፊሊጵስ ዮስ 2፥6-7። እንግዲህ ጌታ ስለሰው ፍቅር ባደረገው የትሕትና ሥራ እንኳን ከአብና ከመንፍስ ቅዱስ፥ከ መላእክትም አንሶ እንደ ነበር መጸሐፍ ቅዱስ ይናገራል። «ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አሰነሳው....» ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አንሶ የነበረውን ኢየሱስ..... ዕብራ.2፥7-9 እን ግዲህ ጥሬ ቃሉን ይዘን ጌታ ከመላእክት ያንሳል ብለን ልንናገር እንደፍራለን? ሐዋርያው ግን ስለ እኛ ያደረገውን ዕጹብ ድንቅ ሥራውን፥ ፍቅሩንና ትሕትናውን ሲገልጽ፥ መላእክትን እንዳይሞቱ አድርጐ የፈ ጠረ አምላክ እሱ ግን ሞተ ብሎ ታላቅ ፍቅሩንና ሰው መውደዱን ገለጸ፤ ወዶ ፈቅዶ በአትሕቶ ርእስ መገለጹን ሲያስረዳ ነውና። ስለዚህ አብና መንፈስ ቅዱስ በተለየ አካላቸው ሥጋን ተዋሕደው መከራን ባለመቀበላቸው ስለሰው ልጆች ፍቅር ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ በሕልውና ሳይለይ መከራንና ውርደትንበ መቀበል በትሕትና በገዛ ፈቃዱ ዝቅ ማለቱን ቢገልጽልን ጊዜ መናፍቃን ልዑልን ኃያሉን ደካማ አደረጉት ፥ እንደ አርዮስም ከባህርይ አባቱ ለይተው ፍጡር አሉት፤ እሱስ ክብር ምስጋና የሚገባው የባህርይ አ ምላክ ነው።

6. <u>**ዮሐንስ ወንጌል**</u> <u>17፥3</u> «... እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆነህ አንተን የላከውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ት ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት» የሚለውን በመጥቀስ ጌታ እውነተኛ አምላክ እንዳልሆነ አብ ብ ቻ እውነተኛ አምላክ እንደሆነ የሚያስተምሩ መናፍቃን አሉ፤ አባባሉ ግን እነሱ እንደሚሉት ሳይሆን « የዘላለም ሕይወት የሚገኝበት ሃይማኖት ይህ ናት። አንተ የባሕርይ አምላክ እንደሆንክ፥ እኔም የባህርይ አምላክ እንደሆንኩ ያውቁ ዘንድ ቢያውቁ እውነተኛ ሃይማኖት ይህች ናት» ጌታ በአንዳንድ ቦታ ላይ አምላክ ወይም እግዚአብሔር ብሎ እንደ ሰው መፀለዩ በእውነት የሰውን ባሕርይ ባሕርዩው ማድረጉን ሊያስረዳ ፈልጐ ነው እንጂ በባህርዩ ከአብ የሚያንስ ሆኖ አይደለም። እንደ ሰው አምላኬ ወይም እግ ዚአብሔር ብሎ ባይፀልይ ኖሮ በእርሱ ዘንድ ትስብእት (ሰውነት) የለም ወይም መለኮት ትስብእትን ው ጦ አጥፍቶታል በተባለ ነበር።ይኸውም በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ «ለአጽድቆተ ትስብእት» ተብሎ ይተረ ጐማል። ይህም ማለት በእውነት አምላክ ሰው እንደሆነ ያስረዳልና።

በዮሐንስ ወንጌል 17፥3 አብ ብቻውን እውነተኛ አምላክ እንደ ሆነ ተገልጿል። በይሁዳ መልዕክ ት 1፥25 ላይ ወልድ ብቸኛ አምላክ ነው ተብሏል። በማቴ.12፥32 ላይ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተደረገ ስ ድብ ብቻ ምህረት እንደማይደረግለት ተገልጿል። የዚህም ምክንያት ሦስት አማልክት አሉ ለማለት ሳይ ሆን በመለኮታዊ ሥልጣን ሥላሴ አንድ ስለሆኑ ነው። የጌታችን እውነተኛ አምላክነትም ዮሐንስ በመልክ ቱ እንዲህ ሲል ገልጾታል። «እርሱ እውነኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው» 1ኛ ዮሐ. 5፥20።

7. **ዮሐንስ ወንጌል** 20፥17 «ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፥ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ»
ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህን በተረጐመበት ሃይማኖተ አበው ገጽ 248 ተመልከት። «ነገር ግን እርሱ በ
ዚህ ክርስቶስ በእውነት ሰው እንደሆነ አስረዳ፥ ዳግመኛም በተነሳ ጊዜ ከዚህ ከአዳም ባሕርይ ሰው መ
ሆኑን አስረዳ፥ ፈጽሞ ከእርሱ ወደ አልተለየው ወደ አብም ከማረጉ አስቀድሞ ለደቀ መዛሙርቱ አምላ
ኬ አምላካችሁ አለ፥ ይህን በሰሙ ጊዜ ይህን የተናገረ ሥጋ ብቻ እንዳይመስላቸው ሰው የሆነ እርሱ እ
ግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ አባቴ ብሎ ከዚህ በኋላ አምለኬ አለ እንጂ፥ እኔስው የሆንኩ አምላክ ነኝ
ና እኔም አንድ ነኝና ይህንንም ያንንም እኔ እላለሁ ይላል»። እንግዲህ ሊቁ እንደገለጽው ጌታከትንሣኤ
ው በኋላ አምላኬ ማለቱ ቅድመ ተዋሕዶ አምላኬ ይል የነበረን ሥጋ አሁንም እንደተዋሐደ ለማስረዳት
ብሎ ነው፥ሥጋ ከመቃብር ቀረ የሚሉ በኋላ ዘመን እንደሚነሱ ያውቃልና እነርሱን መልስ ለማሳጣትና
ከተዋሕዶ በኋላ መለያየት አለመኖሩን ራሱ ጌታ በዚህ ቃል አስረዳን።

በሌላ በኩልም «አባቴ» ያለው ለእርሱ የባሕርይ አባቱ ስለሆነ ነው። «ወደ አባታችሁ ሲል ለ
እኛ የጸጋ አባታችን እንደሆነ ለማስረዳት ነው። «አምላኬ» አለ በሥጋ ይፈጥረዋልና። ጌታ የፈጠረውን
ሥጋ ነውና የተዋሐደው «አምላካችሁ» አለ በጥንተ ተፈጥሮ በሃዲስ ተፈጥሮ ይፈጥረናልና።

8 **1ኛ ቆሮ**.15፥24-28 «በኋላም መንግሥትን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ግዜ አለቅነቱንም ሁ
ሉን ሥልጣንን ሁሉ ኃይልንም በሻረ ጊዜ ፍጻሜ ይሆናል። ሁሉ ነገር ከተገዛለት በኋላ እግዚአብሔር ሁ
ሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያ ጊዜ ወልድ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ተገዥ ይሆናል» ፥ «ሁሉን ላስገዛለት
ተገዥ ያሆናል» የሚለውን በመጥቀስ ወልድ የአብ ተገዥ ነው ይላሉ። ነገር ግን ምስጢሩን ከተመለከ
ትን ከላይ ስለሞት እየተናገረ መምጣቱን እንረዳለን። በኋላ ጠላት የተባለው ሞት ነው። ሞት ሁሉንም
ገዝቷልና፤ ነገር ግን ሁሉን ካስገዛለት ከወልድ ሞት እንዲያንስ ያታወቃል፥ በሁሉ ላይ እንዲሰለጥን ያደ
ረገው ባለቤቱ ነውና፥ ይህስ ቁም ነገር አይደለም ብሎ ካስገዛለትከስው ሁሉ ሞት እንዲያንስይታወቃል
በዕለተ ምጽአት። ሁሉ በተገዛለት ጊዜ ያን ጊዜ ወልድም ሁሉን ላስገዛለት ለሞት ተገዝቷል የዕለተ ዓር
ብን መናገር ነው። በዕለተ ዓርብ በዘጠኝ ሰዐት ቅድስት ነፍሱን ከቅድስት ሥጋው በገዛ ፈቃዱ ለይቶአል
ና፥ ሞት ለሦስት መአልትና ለሦስት ሌሊት ጌታን በቁጥጥሩ ሥር አድርጐ ነበርና ይህም የጌታ ፈቃድ ስ
ለሆነ ነው እንጂ እንደ ሌሎች ሳይወድ በግድ አይደለም።

9. **ቆላ**.1፥15 «.. እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው» የዚህማ አባባል እግዚአብሔርን በመልክ የሚ
መሰለው በባሕርይ የሚተካከለው ለማለት እንጂ አምላክ ያልሆነ አምላክ መስል ለማለት አይደለም።

10. **የሐዋ. ሥራ** 2፥32 «ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሳው.....» እግዚአብሔር ብሎ መለኮትን ለመ
ግለጽ ተጠቀመበት እንጂ አብ ብቻውን ያለወልድና ያለመንፈስ ቅዱስ አስነሺ፥ ወልድ በባሕርይ ሥል
ጣን ከአብ የተለየ ወይም አብ ብቻ ብርቱ ወልድ ግን ለመነሣት ሥልጣን የሌለው ደካማ ነው ማለት አ
ይደለም። ጌታ ኢየሱስ በገዛ ፈቃዱ ለመሞቱናበገዛ ሥልጣኑ ለመነሣቱ በዮሐ. 0፥17-18 ይገልጻል። «ነፍ
ሴንም ስለበጐች አኖራለሁ እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም፥ ላኖራት ሥልጣ
ን አለኝ፥ ደግሞም ላነሳት ሥልጣን አለኝ» ቅዱስ ሉቃስ ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሳው ማለቱ መለ
ኮት የተዋሕደውን ሥጋ አስነሳ ለማለት ፈልጐ መሆኑን ሲያስገነዝበን ነውና በሃሳውያን ስሕተታዊ ትርጉ
ም ወልድ ዋህድ ኢየሱስ ክርስቶስ ዕሩቅ ብእሲ ብሎ ከመካድ እንጠበቅ፥ እንጠንቀቅ።

ከላይ የተጠቀሰው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔርነት አምነን ከሐ
ስተኖች ትምህርት እንጠበቅ ዘንድ ያስገነዝበናል። «ክርስቶስ በሥጋ መጣ፥ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለ
ዘላለም የተባረከ አምላክ ነው አሜን» ሮሜ 9፥5

***ማጠቃለያ***

1. **ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው። በመለኮቱ የእግዚአብሔር ልጅ፥ በሥጋ የአዳም ልጅ እንደሆነ እናምናለን። ሰው ባልሆነ አካል የሰውነት ሥራ አይሠራም ሥጋን ከርሷ የተነሣ ቅድስት ድንግል ማርያም ሞት የሚስማማት ስለሆነች ሞት የሚስማማውን ሥጋ ተዋሕዶአልና። ስለዚህም የተቀበለው ልቅሶ፥ ሕማም፥ ሞት ከድንግል የተነሳው የሥጋ ገንዘብ ነው። አዘነ አለቀሰ ሲል ብትሰማ ያዘነ ያለቀሰ አምላክ ቃል እንደሆነ አታስብ ይህ ሁሉ ሥጋ በመሆኑ ነው እንጂ።**

2. **ይህ ወልድ ለአንድ የምንሰግድለት ለአንዱ የማንሰግድለት ሁለት ባሕርይ ነው የምንል አይደለም። ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ባሕርይ አንድ ስለሆነ ከሥጋው ጋር አዋሕደን አንዲት ስግደት እንሰግድለታለን እንጂ።**

3. **ከእኛ በተነሣው ሥጋ ሞተ በማለት ፋንታ እግዚአብሔር አምላካችን ሥጋ በሌለው ባሕርይ ታመመ ሞተ ይሉት ዘንድ አይገባም።**

4. **ክርስቶስ ፈጣሪ፥ እግዚአብሔር መሆኑን እናምናለን፥ ስለሆነም ፍጡር ነው የሚሉትንና ዛሬም በአብ ቀኝ ተቀምጦ ለእኛ ያማልዳል የሚሉትን እንቃወማለን።**

5. **ወልድ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ አንድነት ሳይለይ በምልአት ሳለ ሥጋ መሆኑ እንደምን ነው**? **ቢሉ የዓይን ብርሃን ከዓይን ብሌን ሳይለይ ከብርሃነ ፀሐይ ጋር ተዋሕዶ ምሉዕ እንደሆነ ጌታም በምልአተ ባህርዩ ሳለ በማህጸነ ድንግል አድሮ ከመቅጽበተ ዓይን ሰው ሆነ። የማይለይ የማይነገር የማይመረመር ተዋህዶ ሆነ።**

**ዓምደ ሃይማኖት ከሚለው ብርሃኑ ጎበና በ**1992 **ካሳተሙት የተወሰደ።**

www.ethiopianorthodox.org